SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

2ki Diro Kiiro 20 Hawaasa, Sadaasa 23, 2014 M.D	Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳ ሀዋሳ፣ ታህሳስ ፳፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

Amado

Lallawu Kiiro 20/2014

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Quchumma Wirro Uurrisatenna Tantanate, Biilloonyensanna Loosu Qeechansa Murate Fulino Lallawa … Qoola ….

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳/፳፻፲፬

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከተሞችን እንደገና ለማቋቋምና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸዉን ለመወሰን የወጣ አዋጅ … ገጽ ….

Lallawu Kiiro 20/2014

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Quchumma Wirro Uurrisatenna Tantanate, Biilloonyensanna Loosu Qeechansa Murate Fulino Lallawa

Qoqqowoho quchummate dancha gashshoote tuqisatenninna wo'munka hanqafino latishsha buuxisatenni quchumma laalchunnita, owaantennitanna dikkote mereersha ikkite qoqqowunnita industirete latishsha jawu deerrira reekkate lowo qeechi hee'rannonsa gede assa hasiissinohura;

አዋጅ ቁጥር ፳/፳፻፲፬

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከተሞችን እንደገና ለማቋቋምና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በክልሉ በከተሞች መልካም አስተዳደር በማስፈን እና ሁሉን አቀፍ ልማት በማረጋገጥ ከተሞች የምርት፣ የአገልግሎትና የገበያ ማዕከላት ሆነው የክልሉን የኢንዱስትሪ ልማት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር የላቀ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፤

Qoqqowu giddo heedhanno quchumma rakkino mannu kiiro lopho ledo xaaddanno garinni lifixanna taalcho maazzagaajju mini owaante uynanni gara jawaachishanna faajjetenna xa'mamooshshu noo loosu amuraate diriirsa latishshu rankeranna dimokraasete ha'rinsho kaajjishate jawu qeechi noosiha ikkasinni;

Quchummate hala'la garinni quchumu teessaano beeqqooshshenna horaamimma buuxisate dandiisiisanno kuusaminokki gashshoote kaajjishate gobboomu quchummate deerri bikkaanchi garinni qoqqowu quchummate deerra gaamate bikkaanchinna quchummate nooha danchu gashshooti qarra tirate dandiisissano tantano diriirsa hasiisannohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Bayriidi Seeri quwa 48(3) (a) garinni aane nooha lallamboonni.

FOOLIISHSHO MITE

Xaphooma Woro

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Quchumma Wirro Uurrisatenna Tantanate, Biilloonyensanna Loosu Qeechansa Murate Fulino Lallawa Kiiro 20/2014" yine woshshinara dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu horosi garinni wole tiro uysiisannoha ikka hoogiro konni lallawira:

   1. **"Bayriidi Seera"** yaa Sidaamu Dagoomu

በክልሉ በሚገኙ ከተሞች ከፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር በተጣጣመ መልኩ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈን እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ለልማት መፋጠንና ለዴሞክራሲ ግንባታ መጠናከር ጉልህ ፋይዳ ያለው በመሆኑ፤

ከከተማነት መስፋፋት አንፃር የከተማ ነዋሪዎችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከር ከሀገራዊ የከተሞች ፈርጅ መስፈርት አኳያ ክልሉ የከተሞች ደረጃ ምደባ መስፈርት እና በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አደረጃጀት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከተሞችን እንደገና ለማቋቋምና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡-

Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seeraati.

2. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
3. **“Biiro”** yaa Quchumu Latishshinna Konistiraakishiinete biirooti.
4. **“Quchuma”** yaa lamu kuminna hakonni ale ikkitino teessaano noosihu; xibbunni ontawo anga ale giwirinnu loosi gobbaanni noo loosinni galtino daga heedhanno seerunni quchumimmate afamooshshe afi’rino dagoomu teesso qooxeessaati.
5. **“Sinu Quchuma”** yaa rejiopoosili quchuminni kayise deerra lamu quchumi geeshsha nooha ikke teessaanote dagoomitte owaante iillishate yine quchumu gashshooti woroonni olluubbate aleenni hige tantanamino quchumu bisooti.
6. **“Dagate Batinye”** yaa seerunni quchumimmate afamooshshe uynoonninna quchumimmate qoqqomboonni qooxeessira afantanno xaphooma quchumu teessaano kiirooti.
7. **“Deerra”** yaa quchumma polotikunni, miinjunninna dagoomu latishshi millimmo garinni iillitino lophote deerra keenate qixxaabbino safaraanonni abbitino xaphoomu gumi garinni uynoonninsa quchumimmate deerraati.
8. **“Quchumu Amaale Mine”** yaa quchumimmate qoqqomboonni qooxeessira dagate doorshinni uurrinsanni seera fushshanno mootimmate biilloonyi bisooti.
9. **“Rejiyopoolis Quchuma”** yaa quchummate latishsha rahisate widoonni lophote

1. **“ሕገ መንግሥት” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ሕገ መንግሥት ነው።**
2. **“ክልል” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው።**
3. **“ቢሮ” ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ነው።**
4. **“ከተማ” ማለት ሁለት ሺህ እና ከዚያ በላይ ነዋሪ ያለው፣ ሀምሳ ከመቶ በላይ ከግብርና ሥራ ውጪ በሆኑ የሥራ መስኮች የተሰማራ ሕዝብ የሚኖርበት በሕግ የከተማነት እውቅና የተሰጠው የጎበረተሰብ መኖሪያ አካባቢ ነው።**
5. **“ክፍለ ከተማ” ማለት ከሬጂዮፖሊስ ከተማ እስከ ፈርጅ ሁለት የከተማ አገልግሎቶችን ለነዋሪው ሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ ከከተማ አስተዳደር በታች ከቀበሌያት በላይ የሚዋቀር የከተማ አካል ነው።**
6. **“የሕዝብ ብዛት” ማለት በሕግ የከተማነት ዕውቅና በተሰጠው እና በከተማነት በተካለለ አካባቢ የሚገኝ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ነው።**
7. **“ፈርጅ” ማለት ከተሞች በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማኅበራዊ ልማት እንቅሰቃሴ ሂደት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ለመመዘን ከተዘጋጁት መስፈርቶች አንጻር ባመጡት ድምር ውጤት መሠረት የተሰጣቸው የከተማነት ደረጃ ነው።**
8. **“የከተማ ምክር ቤት” ማለት በከተማነት በተካለለው አካባቢ በሕዝብ ምርጫ የሚቋቋም ሕግ አውጪ የመንግሥት ሥልጣን አካል ነው።**
9. **“ሬጂዮፖሊስ ከተማ” ማለት የከተሞችን ልማት ከማፋጠን አንፃር የልማት ማዕከል በመሆን በዙሪያቸው ያሉትን**

mereersha ikkatenni qooxeessaho noo quchumma amadde lophate doorantino hala'lado quchummara uynoonni su'mishshaati.

10. **"Quchumu Gashshoote"** yaa bande anfoonni faronni tantanamino polotiku, miinjunna dagoomu latishshanna owaante uynanni gara massagate biilloonyenna yawo seerunni uynoonni quchumaati.
11. **"Uurrinshu Yoo Mine"** yaa quchummate tantanamanno umi dirimi yoo mine woy aliidi yoo mineeti.
12. **"Quchuma Labbanno Hajubba Gashshooti Yoo Mine"** yaa quchuma labbanno hajubba la"ate quchummate uurrinsanni gashshootu yoo mineeti.
13. **"Maazzegaajju Minna Owaante"** yaa quchummate teessaano daga hasatto kassi assatenna dagoomittenna miinju qarrubba tirate widoonni baalunku quchumira uynanni quchumma labbanno owaanteeti.
14. **"Kantiiba"** yaa quchumu amaale mininni woy qeeltino poletiku paartenni doorranniha ikke quchumunniha poletiku, miinjunna dagoomitte hajubba; hattono danchu gashshootinna quchumu owaante aliidimmatenni massagannonna loosu aana hosiisanno quchumu qara loosu jeefissisaanchooti.
15. **"Kantiibu Komite"** yaa quchumu gashshooti amaale mineeti.
16. **"Loosu Ha'risaancho"** yaa deerru deerrunkunni noo quchummara ogimmate dandoonninna quchumu looso massagate

ከተሞች ይዘው እንዲያድጉ ለተመረጡ ሰፋፊ ከተሞች የተሰጠ ስያሜ ነው።

10. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት ተለይቶ በታወቀ ወሰን የተደራጀ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ለመምራት ሥልጣንና ኃላፊነት በሕግ የተሰጠው ከተማ ነው።
11. **"መደበኛ ፍርድ ቤት"** በከተሞች የሚደራጅ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይንም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው።
12. **"ከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት"** ማለት የከተማ ነክ ጉዳዮችን እንዲያይ በከተሞች የሚቋቋም አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ነው።
13. **"ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት"** ማለት የከተሞችን ነዋሪ ኅብረተሰብ ፍላጎት ከማርካትና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ከመቅረፍ አንፃር በሁሉም ከተሞች የሚሰጥ የከተማ ነክ አገልግሎት ነው።
14. **"ከንቲባ"** ማለት ከከተማው ምክር ቤት ወይንም ከአሸናፊ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመረጥ የከተማውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር እና የከተማ አገልግሎት ሥራዎችን በበላይነት የሚመራና የሚያስተገብር የከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው።
15. **"የከንቲባ ኮሚቴ"** ማለት የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ነው።
16. **"ሥራ አስኪያጅ"** ማለት በየደረጃው ባሉ ከተሞች በሙያ ችሎታና በከተማ ሥራ አመራር ረገድ በላቀ የትምህርት ዝግጅትና

widoonni jawa rosu qixxaawonna ikkado loosu rosicho kaima assatenni biiloonsinanni quchumu owaante loosi sooreessaati.

17. **“Seeru Mannimma”** yaa konni lallawira quchumimmate tantanantino daga heedhanno qooxeessira uynanni uurrinshate afamooshsheeti.
18. **“Quchumu Ollaa”** yaa quchummate shiimiidi gashshootu dirimaati.
19. **“Qacha”** yaa konni lallawi garinni quchummate wo’ma dagate beeqqo lossate uynanni dagate tantanooti.
20. **“Qooxeessa’’** yaa quchummate dagannita latishshu beeqqooshshe lossate qachu woroonni tantannanni dagate beeqqooshshi tantanooti.
21. **“Xaawa”** yaa qachaho woroonni dagannita latishshu beeqqooshshe busulsatenna lossate tantannanni dagate tantanooti.
22. **“Keerunna Latishshu Amaalaancho Amaale Mine”** yaa quchumu qachi deerrinni teessaano keerunna latishshaho heedhanonsa beeqqo lossate ollu gashshootinni uurranno amaalaancho amaale mineeti.
23. **“Keerunna Latishshu Komite”** yaa quchumu qachi deerrinni uurrino keerunna latishshu amaalaancho amaale minira hundaancho ikke teessaano dagoomi keerunna latishshaho beeqaancho ikke loosanno loossa jeefisiisanno tantanooti.
24. **“Baadiyyete Owaantete Mereersha”** yaa qoqqowu baadiyyete olluuba hundaanni hee’ranno quchumimmatenni

በዳበረ የሥራ ልምድ ላይ ተመስርቶ የሚሾም የከተማ አገልግሎቶችን የሚያከናውን ኃላፊ ነው።

17. **“የሕግ ሰውነት”** ማለት በዚህ አዋጅ በከተማነት ለተደራጀ ማኅበረሰብ መኖሪያ አካባቢ የሚሰጥ ተቋማዊ ዕውቅና ነው።
18. **“የከተማ ቀበሌ”** ማለት በከተሞች ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ነው።
19. **“ቀጠና”** ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በከተሞች ሁለንተናዊ የሕዝብ ተሳትፎን ለማሳደግ የሚፈጠር የሕዝብ አደረጃጀት ነው።
20. **“ሠፈር”** ማለት በከተሞች የሕዝብ ልማታዊ ተሳትፎን ለማጎልበት ከቀጠና በታች የሚደራጅ የሕዝብ ተሳትፎ አደረጃጀት ነው።
21. **“ጣቢያ”** ማለት ከሰፈር በታች የሕዝብ ልማታዊ ተሳትፎን ለማሳለጥና ለማጎልበት የሚደራጅ የሕዝብ አደረጃጀት ነው።
22. **“የሰላምና ልማት አማካሪ ምክር ቤት”** ማለት በከተማ ቀጠና ደረጃ ነዋሪው በሰላምና ልማት የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግ በቀበሌ አስተዳደር አማካይነት የሚመሰረት አማካሪ ምክር ቤት ነው።
23. **“የሰላምና ልማት ኮሚቴ”** ማለት በከተማ ቀጠና ደረጃ በተቋቋመ የሰላምና ልማት አማካሪ ምክር ቤት ተጠሪ ሆኖ ነዋሪው ሕዝብ በሰላምና ልማት ተሳታፊ ሆኖ የሚሰራቸውን ተግባራት የሚያስፈጽም አደረጃጀት ነው።
24. **“የገጠር አገልግሎት ማዕከል”** ማለት በክልሉ የገጠር ቀበሌያት ሥር የሚገኝ በከተማነት ያልታቀፈ ለአካባቢው የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ የገበያ ማዕከል

hanqafaminokki qooxeessaho addi addi owaante shiqishatenni dikkote mereersha ikke quchumu-baadiyyete xaadooshshe rahisatenni horo aanno quchuma lawanno qooxeessaati.

25. **"Quchumu Gashshooti Danna"** yaa biilloonye uynoonnsi bisinni badaminonna quchumu gashshooti hundaanni amadamino qooxeesaati.
26. **"Quchumu Pilaane Danna"** yaa mittu quchumira quchumu pilaane garinni bikkantino pilaanete woggara kaartunni badamino quchumu baattote horo dannaati.
27. **"Dagoomitte Yoo Mine"** yaa hasiishshu garinni quchumu olliira uurranno yooaanchimmate bisooti.
28. **"Mancho"** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso uynoonni bisooti.

3. Koo-teemmate Xawishsha

Konni lallawi giddo mitte kooteemmanni xawinsoonnihu wole koo-teemmano hanqafanno.

4. Jeefishshu Mami-Geeshsha

Kuni lallawi qoqqowu giddo uurritinonna uurritanno quchumma gashshootiranna maazegaajju mini quchumma baalantera loosu aana hosanno.

FOOLIISHSHO LAME

Quchummate Deerranna Hundaanchimma

5. Quchummate Deerra

ሆኖ የከተማ–ገጠር ትስስርን በማፋጠን የሚያገለግል ከተማ ቀመስ አካባቢ ነው።

25. **"የከተማ አስተዳደር ወሰን"** ማለት ሥልጣን በተሰጠው አካል የተካለለ እና በከተማው አስተዳደር ሥር የተጠቃለለ አካባቢ ነው።
26. **"የከተማ ፕላን ወሰን"** ማለት ለአንድ ከተማ በከተማ ፕላን መሠረት ለተወሰነ የፕላን ዘመን በካርታ የተካለለ የከተማው የመሬት አጠቃቀም ወሰን ነው።
27. **"ማኅበራዊ ፍርድ ቤት"** ማለት እንደ አስፈላጊነቱ በከተማ ቀበሌ የሚቋቋም የዳኝነት አካል ነው።
28. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል።

4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ በተቋቋመ እና በሚቋቋሙ ከተማ አስተዳደሮች እና ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

ምዕራፍ ሁለት

የከተሞች ፈርጅ እና ተጠሪነት

5. የከተሞች ፈርጅ

1. የክልሉ ከተሞች በደረሱበት የእድገት ደረጃ

1. Qoqqowu giddo noo quchumma iillitino lophote deerrinninna fultanno safaraano kaima assatenni aantanno quchummate deerri giddonni mittoho gaamantara dandiitanno:
   a) Regiopolis
   b) Deerra mite
   c) Deerra lame
   d) Deerra sase
   e) Deerra shoole
   f) Deerra onte
2. Regiopolisete quchumi, deerra mittunna deerra lamu quchummara sinu quchumi, quchumu ollii gashshootinna qachu tantano heedhannonsa.
3. Deerra sasu aana noo quchummara quchumu ollii gashshootinna qachu tantano heedhannonsa.
4. Deerra shoolenna deerra ontete quchummara quchumu ollii gashshooti hee'rannonsa.
5. Quchummate ollii gashshooti tantanonna deerru wodhotenni gumulantanno.
6. Wo'munku deerrira heedhanno quchummara daganniha latishshu beeqqooshshe bowirsate qachu, xaawunna daganniti latishshu beeqqooshshi tantano heedhansara dandiitanno. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.
7. Regiopolisete, deerra mittunni kayse deerru ontu geeshsha heedhannoti quchummate olluubba olluu gashshaanchinni massagantannoha ikkanna deerrinsa garinni mootimmate tantano heedhannonsa.

እና በሚወጣዉ መስፈርት ላይ በመመስረት ከሚከተሉት የከተማ ፈርጆች በአንዱ ሊመደብ ይችላል፡-

ሀ) ሬጂዮፖ'ሊስ፣

ለ) ፈርጅ አንድ፣

ሐ) ፈርጅ ሁለት፣

መ) ፈርጅ ሶስት፣

ሠ) ፈርጅ አራት፣

ረ) ፈርጅ አምስት፣

2. **የሬጂዮፖ'ሊስ ከተማ፣ ፈርጅ አንድ እና ፈርጅ ሁለት ከተሞች ክፍለ ከተማ፣ የከተማ ቀበሌ አስተዳደር እና ቀጠና አደረጃጀት ይኖራቸዋል።**

3. **ፈርጅ ሶስት ላይ ያሉ ከተሞች የከተማ ቀበሌ አስተዳደር እና የቀጠና አደረጃጀት ይኖራቸዋል።**

4. **ፈርጅ አራት እና ፈርጅ አምስት ከተሞች የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ይኖራቸዋል።**

5. **የከተሞች ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት እና ደረጃ በደንብ ይወሰናል።**
6. **በሁሉም ፈርጆች በሚገኙ ከተሞች የሕዝብ የልማት ተሳትፎን ለማጎልበት የሠፈር፣ የጣቢያ እና የሕዝብ የልማት ተሳትፎ አደረጃጀቶች ሊኖራቸው ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።**
7. **በሬጂዮፖ'ሊስ፣ ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ አምስት የሚገኙ የከተማ ቀበሌያት በቀበሌ አስተዳዳሪ የሚመሩ ሆነው እንደየደረጃቸው መንግሥታዊ መዋቅር ይኖራቸዋል።**

6. Quchummate Deerra Keennanni Safaraanchi

Quchummate deerrinna keennanni safaraano wodhotenni gumulantanno.

7. Hundaanchimma

Quchummate hundaanchimma biilloonyu hoode deerri aana kaima assitinotanna mittu mittunku quchumma teessaano dagara ikkite:

1. Regiopolise quchumi hundaanchimma qoqqowu mootimmara ikkitanno;
2. Deerra mittunni kayse deerra sasu geeshsha noo quchumma hundaanchimma zoonete gashshootira ikkitanno;
3. Deerra shoolunna deerra ontu quchumma hundaanchimma heedhanno woradi gashshootira ikkitanno.

8. Quchumimmatenni Uurrra

1. Ayee dagoomi teesso qooxeessi quchumimmate afamooshshe afi'ra dandaannohu biiro quchumimmatenni uurrissusiro callaati.
2. Quchumimmate afamooshshe afi'ra dandiinannihu daga biirote shiqishshanno xa'monni woy biiro umise kakkaooshshinni quchumimmate afamooshshe xiinxallo assite uytano gumulonniiti.
3. Biiro ku'laato haadhuhu gedensaanni safaraanchu guutasi buuxxuro gumulo uytanno.
4. Quchumimmate seeru mannimma afi'rate shiqqino xa'mo dawaro afi'ra hoogguro korkaata borrotenni xawinse xa'mo shiqishi

6. የከተሞች ፈርጅ መመዘኛ መስፈርት

የከተሞች ፈርጅ እና መመዘኛ መስፈርቶች በደንብ ይወሰናል።

7. ተጠሪነት

የከተሞች ተጠሪነት በሥልጣን ተዋረድ ደረጃ ላይ የተመሰረተ እና ለየከተማው ነዋሪ ሕዝብ ሆኖ፡-

1. **የሬጂዮፖሊስ ከተማ ተጠሪነቱ ለክልሉ መንግሥት ይሆናል፤**
2. **ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ ሶስት ድረስ ያሉ ከተሞች ተጠሪነታቸዉ ለዞን አስተዳደር ይሆናል፤**
3. **የፈርጅ አራት እና ፈርጅ አምስት ከተሞች ተጠሪነታቸው ለሚገኙበት ወረዳ አስተዳደር ይሆናል።**

8. በከተማነት ስለመቋቋም

1. **ማንኛውም ማኅበረሰብ መኖሪያ አካባቢ የከተማነት እውቅና ሊያገኝ የሚችለው ቢሮው በከተማነት ሲያቋቁመው ብቻ ነው።**
2. **የከተማነት እውቅና ማግኘት የሚቻለው ማኅበረሰቡ ለቢሮው በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ቢሮው በራሱ ተነሳሽነት የከተማነት እውቅና በማጥናት በሚሰጠው ውሳኔ ነው።**
3. **ቢሮው ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ መስፈርቱ መሟላቱን ሲያረጋግጥ ውሳኔ ይሰጣል።**
4. **የከተማነት ሕጋዊ ሰዉነት ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ ምክንያቱ**

bisira woy lekkisaanote dawaro aamama noosi.

5. Quchumu afamanno base lamu woradi gashshooti faro aana ikkiro hundanchimma gumullannihu lamunku woradi hundaancho ikkitino zoonete gashshootira ikkanna lame zoonna gashshooti giddo ikkiro hundaanchimma gumullannihu qoqqowu gashshootu amaale minira ikkanno.

9. Seeru Mannimma Afi'ra Lainohunni

Konni lallawi garinni quchumimmate afamishsha uynoonni dagoomi teesso qooxeessi:

1. Umisi seeru mannimma noo biso ikke hakko su'minni woshshamate;
2. Sheemaate eate, jajju anna ikkatenna jajjasi gashshate, qaxxaro shiqishatenna qaxxaro shiqqasira seeru dandoo heedhannosi.

10. Seeru Mannimma Kaysa

1. Quchumunniti seeru mannimma ka"a dandiitannohu quchumimmate safaraano wonshe sufa dandaa hoogasi xiinxallotenni buunxe biirotenni gumulliro ikkanno.
2. Quchumunniti seeru mannimma ka'ara albaanni afantino qoossubbanna gadachubba gashshootu biilloonyinna loosu qeechi ha'rino bisira sa'anno.

11. Quchumu Su'mu Soorro Assa Lainohunni

1. Mittu quchumi su'mi soorro assa dandiinannihu quchumu teessaanonni iillinoonni sumuumme quchumu amaale

በጽሁፍ ተገልጾ ጥያቄዉን ላቀረበ አካል ወይም ለተወካዮቻቸዉ መልሱ መሰጠት አለበት፡፡

5. **የከተማው መገኛ ስፍራ በሁለት ወረዳዎች አስተዳደር ወሰን ላይ ከሆነ ተጠሪነቱ የሚወሰነው ሁለቱም ወረዳዎች ተጠሪ በሆኑለት የዞን አስተዳደር ሲሆን በሁለት ዞኖች አስተዳደር ወሰን ውስጥ ከሆነ ተጠሪነቱ የሚወሰነው በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡**

9. የሕግ ሰውነት ስለማግኘት

በዚህ አዋጅ መሰረት የከተማነት እውቅና የተሰጠው የማኅበረሰብ መኖሪያ አካባቢ፡-

1. **የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚያ ስም የመጠራት፣**
2. **ውል ለመዋዋል፣ የንብረት ባለቤት ለመሆንና ንብረቱንም ለማስተዳደር፣ ለመክሰስና ለመከሰስ የሕግ ችሎታ ይኖረዋል፡፡**

10. የሕግ ሰውነትን ስለመሠረዝ

1. **የከተማ የሕግ ሰውነት ሊሠረዝ የሚችለው የከተማነት መስፈርቶችን አሟልቶ መቀጠል የተሳነው መሆኑን በጥናት ተረጋግጦ በቢሮ ሲወሰን ይሆናል፡፡**
2. **የከተማው ሕጋዊ ሰውነት ከመሠረዙ በፊት የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች የአስተዳደር ሥልጣንና ተግባሩ ወደተላለፈበት አካል ይሸጋገራሉ፡፡**

11. የከተማ ስም ለውጥ ስለማድረግ

1. **የአንድ ከተማ ስም ለውጥ ማድረግ**

mininni, quchumu hundaancho ikkino gashshooti taqqinni woy gashshootu amaale mininni maahoyye afi'rirooti. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

2. Danna xaaddanno quchumma teessaanote sumuumme garinni xaadde mittu su'minni woshshantara dandiitanno.
3. Konni quwira cinaancho quwa 2 xawinsoonnihu noo gedeenni hee'reenna quchumu su'mu soorro kaajjitannohu gumulo biiroteninna karsamino quchumi hundaancho ikkino gashshootu bisi wonsironna affini gaazeexinni lallawamiro ikkanno.
4. Konni quwira cinaancho quwa 1 nna 2 garinni su'mu soorro assinoonniha ikkiro albiidi su'minni afi'rino qoossubbanna gadachubba haaru su'mi widira sa'anno.

FOOLIISHSHO SASE

Quchummate Biilloonyenna Loosu Qeecha

12. Quchummate Biilloonyenna Loosu Qeecha

1. Qoqqowu quchumma konni lallawinni bande uynoonninsa hajubba aana seera fushshate; seera jeefissisatenna yooaanchimmate biilloonyi noonsa.
2. Konni quwira cinaancho quwa 1 xaphooma woro noo gedeenni heedheenna quchumma konni woroonni tittirotenni worroonni biilloonyinna loosu qeechi hee'rannonsa:
   a) Ajuuja, hexxonna loosu qeecha hattono garimma noonsa jeefishshu hayyo gumultanno; loosu aana hosiissanno;

የሚቻለው በከተማው ነዋሪዎች የተደረሰው ስምምነት በከተማው ምክር ቤት፣ ከተማው ተጠሪ በሆነለት የአስተዳደር እርከን ወይም መስተዳድር ምክር ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ ነው። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. ኩታ ገጠም የሆኑ ከተሞች በነዋሪዎቻቸው ስምምነት መሰረት ተዋህደው በአንድ ስም ሊጠሩ ይችላሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተሞቹ የስም ለዉጥ የሚጸናው ውሳኔው በቢሮው እና የተዋሄደው ከተማ ተጠሪ በሆነበት አስተዳደር አካል ሲጸድቅ እና በአፍኒ ጋዜጣ ሲታወጅ ይሆናል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የስም ለውጥ የተደረገ እንደሆነ በቀድሞ ስም የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች ወደ አዲሱ ስም ይሸጋገራሉ።

ምዕራፍ ሦስት

የከተሞች ሥልጣንና ተግባር

12. የከተሞች ሥልጣን እና ተግባራት

1. የክልሉ ከተሞች በዚህ አዋጅ ተለይተው በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነት እና የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች ከዚህ በታች በዝርዝር የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-
   ሀ) ራዕዩን፣ ዓላማውን እና ተግባራቱን እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን

b) Gobbanniha, qoqqowu seeranna wolootu hajo la'anonsa bissa fushshitino seera gurchannokki garinni qooxeessu seerubba fushshitanno; hajubbate aana gumulo uytanno; dancha gashshoote kalaqqanno; buuxissanno;

c) Qoqqowu seeri garinni umisi baajeette gashshitanno;

d) Qoqqowu mootimma fushshitanno faynaansete seeri garinni quchumu eote buicho gumultanno; gabbaro, taarifenna owaantete baatooshshe woyyeessitanno; halashshitanno; gamba assitanno; quchumu latishshira hosiissanno; la'annonsa bissa fajjituro liqoo liqiidhanno;

e) Hajo la'annonsa bissa affanno gede assite gobbate giddonna baara widi quchumma ledo rodiimmate xaadooshshe kalaqqanno; konni lallawinna wolootu seerubba garinni sumuumme assitanno;

f) Dagate horora hasiisannota ikkitino quchumu baatto amado aana noo hallanyu jajjira seeru garinni balaxe ikkado kiiso baatatenni dagate horora hossanno gede assitanno;

g) Teessaanote deerra agadhinoha mazzagaajju mininna mootimmate owaante shiqishshanno woy shiqase buuxxanno;

h) Keerunna ammanchishshanno ga'labbo noota dimokiraasete amuraati lopho kaajishshannota hallanyu uurrinshubba; sivike maamarranna dagannihu

የአፈፃጸም ስልቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የሀገሪቱን፣ የክልሉን ሕጎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ያወጧቸውን ሕጐች የማይቃረኑ አካባቢያዊ ሕጎችን ያወጣል፤ በጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ መልካም አስተዳደር ያሰፍናል፤ ያረጋግጣል፤

ሐ) በክልሉ ሕግ መሰረት የራሱን በጀት ያስተዳድራል፤

መ) የክልሉ መንግሥት በሚያወጣው የፋይናንስ ሕግ መሠረት የከተማውን ገቢ ምንጭ ይወስናል፤ ግብር፣ ታሪፍ እና የአገልግሎት ክፍያ ያሻሽላል፤ ያሰፋል፤ ይሰበስባል፤ ለከተማው ልማት ያውላል፤ አግባብ ያለው አካል ሲፈቅድ ብድር ይበደራል፤

ሠ) አግባብ ያለው አካል እንዲያውቅ በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ከተሞች ጋር እህትማማች ግንኙነት ይፈጥራል፤ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሰረት ስምምነት ያደርጋል፤

ረ) ለሕዝብ አገልግሎት አስፈላጊ በሆነ የከተማ ይዞታ ላይ ለሰፈረው የግል ንብረት በሕግ መሰረት በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ በመክፈል ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፤

ሰ) ለነዋሪው ስታንዳርዱን የጠበቀ ማዘጋጃ ቤታዊ እና መንግሥታዊ አገልግሎት ያቀርባል ወይም መቅረቡን ያረጋግጣል፤

ሸ) ሰላምና አስተማማኝ ፀጥታ የሰፈነበት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን

latishshaamu beeqqooshshi bowiranno gede assitanno;

i) Quchummate sagalete woowenna loosu kalaqo; shiimmammaaddu; manaaddunna mereerima interprayzenna industirete latishshi loossa kaajjitanno gede injo kalaqqanno; hasiissanno kaa'lonna irko assitanno;

j) Qoqqowu pilaanete inistituute ledo halamatenni quchumu pilaane loosu aanano hosiissanno;

k) Quchumu pilaane qixxaawonna loosu aana hosiinsanni gari 30% haanju latishshira, 30% xintu latishshi diriirsaranna 40% ijaarshu bikki wodhi woro hedote giddo worinoha ikkasi buuxxanno; tittirshu wodhotenni gumulamanno;

l) Qinaawino xintu latishshinna pilaanetenni massagantanno gede assitanno; way, caabbichunna silkete shiqishsha injeessitanno;

m) Gashshootunna pilaanete danna baddanno; la'annonsa mootimmate bissa ledo qoqqobbanno; tittirshu wodhoteni gumulamano.

n) Ayee ijaarshi garimma afi'rino seera agarinohanna quchumu; qooxeessunna dagoomu hobbaate hattono biinfille agarino garinni quchumunnita massagaancho pilaane safaraano garinni loosamansa ha'runsitanno; buuxxanno;

o) Qoqqowu mootimma minnate latishshi polise garinni quchumu teessaano minu

የሚያጠናክር የግሉ ሴክተር፣ የሲቪክ ማኅበራት እና የሕዝብ ልማታዊ ተሳትፎ እንዲጎለብት ያደርጋል፤

ቀ) በከተሞች የምግብ ዋስትናና የሥራ ፈጠራ፣ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ እና የኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች እንዲጠናከሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ አስፈላጊውን እገዛ እና ድጋፍ ያደርጋል፤

በ) ከክልሉ የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የከተማውን ፕላን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ተ) የከተማ ፕላን ዝግጅቱና አተገባበሩ 30% ለአረንጓዴ ልማት፣ 30% ለመሠረተ ልማት ዝርጋታ እና 40% ለግንባታ ምጣኔ መርህን ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

ቸ) በተቀናጀ መሠረተ ልማትና ፕላን እንዲመሩ ያደርጋል፤ የውሃ፣ የመብራት፣ የስልክ አቅርቦትን ያመቻቻል፤

ኀ) የአስተዳደርና የፕላን ወሰን ይለያል፤ ከሚመለከታቸዉ መንግሥታዊ አካላት ጋር ያካልላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

ነ) ማናቸውም ግንባታዎች አግባብነት ያለውን ሕግ የጠበቀ እና የከተማውን፣ የአካባቢውንና ማኅበራዊ ደህንነት እንዲሁም ውበት በጠበቀ መልኩ የከተማውን መሪ ፕላን መስፈርቶች ተከትለው መገንባታቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

latishshi hasatto wonshate wo'naalsha assitanno; minnate latishshi loossa massagganno; loosu aanano hosiissanno;

p) Quchumu baatto latissanno; lattino baatto shiqishshanno; baatto la'anno taje qineessitanno; gashshitanno;

q) Haanja latishsha hala'lishshanno; dagate gangalatu dargubba owaante shiqqanno gede assitanno; du'namaanchunna moolu ishini amadooshshenna hunnanni amuraate diriirsitanno; lolahu dano yaaddo gargartanno;

r) Dubbu kayishsha, bushshunna dubbu saada latishsha labbannore quchummate qooxeessi agarooshshi loossa loossanno; loosu aana hosaseno buuxxanno;

s) Qeeru, ambulaansetenna giirate dano gargarooshshi owaante aamantanno gede assitanno; waammate baychi owaante injeessitanno; shiqishshanno;

t) Teessaanote teesso qarriweelo afi'nannitanna daga addi addi owaante qarrantukkinni afi'dhannota yannilicho loosu amuraate diriirsitanno;

u) Quchumu giddo ha'rinsanniti daddalu loossa mootimmate seerubbanna wodhubba agarino garinni loosamansanna deerransa agadhitino laalchubbanna owaante horonsidhanno dagara shiqansa ha'runsitanno; buuxxanno;

v) Dureeyyete injo kalaqatenni investimente halashshitanno;

w) Quchummate daa"ataano goshooshannori

ኘ) በክልሉ መንግሥት የቤት ልማት ፖሊሲ መሠረት የከተማውን ነዋሪዎች የቤት ልማት ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ያደርጋል፤ የቤት ልማት ሥራዎችን ይመራል፤ ይተገብራል፤

አ) የከተማ መሬት ያለማል፤ የለማ መሬት ያቀርባል፤ መሬት ነክ መረጃ ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤

ከ) የአረንጓዴ ልማት ያስፋፋል፤ ለኅብረተሰቡ የመዝናኛ እና መናፈሻ አገልግሎት እንዲቀርብ ያደርጋል፤ የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የጎርፍ አደጋ ሥጋትን ይከላከላል፤

ኸ) የደን ተከላ፣ የአፈር እና የዱር እንስሳት ልማት የመሳሰሉ የከተሞች አካባቢ ጥበቃ ተግባራትን ያከናውናል፤ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

ወ) የቁራ፣ የአንቡላንስ እና እሳት አደጋ አገልግሎቶች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ የዘላቂ ማረፍያ አገልግሎቶችን ያመቻቻል፤ ያቀርባል፤

ዐ)የነዋሪዎች አድራሻ በቀላሉ የሚገኝበትንና ኅብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ያለችግር የሚያገኙበትን ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

ዘ) በከተማ ውስጥ የሚካሄዱ የንግድ ሥራዎች የመንግሥት ሕጎችንና ደንቦችን በተከተለ አግባብ መከናወናቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ምርቶችና አገልግሎቶች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ መቅረባቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

tantanamanno gede, xaggetenna budu donna agarantanno gede assitanno;

x) Isilanchimma agarino rosi quchummate hala'lanno gede assitanno;

y) Gargarooshshe kaima assinoha fayyimmate agarooshshi owaante hala'lishshanno; teessaano daga addi addi taraawanno dhibbinni agaramansa buuxxanno;

z) Wedellu mereershubba, ispoortete dargubbanna dagagannita maxaaffate minna hala'litanno gede assitanno;

aa) Quchummate teessaano latishshu beeqqooshshe lossitanno; baxxinohunni wedellunna meentu beeqqooshshenna horaamimma kaajjishshanno; buuxxanno; hattono geerru, bisu xe'ne noonsarinna lossannohu nookki qaaqquulli agarooshshe afi'dhanno gara injeessitanno;.

bb) Quchumunnita seeda yanna mixo, latishshu pirogiraammanna pirojektete qixxaawonna assoote ha'runsitanno;

cc) Quchumunnita hodhishshu owaante yannillicho assitanno; teessaanote hasiissanno owaante aamamase buuxxanno;

dd) Quchumaho hasiisaancho ikkito borreessishshi amuraati diriirinotanna loosu aana hosasi buuxxanno;

ee) Gashshotu amadosi giddo afantanno baato amadooshshe, agarooshshe, horonna xaphooma gashshootu amuraate garumma afidhino goboomunna

ገ) ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ያስፋፋል፤

የ) በከተሞች የቱሪስት መስህቦች እንዲደራጁ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

ደ) ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በከተማዉ እንዲረጋገጥ እና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ጀ) መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ያስፋፋል፤ ነዋሪው ጎብረተሰብ ከተለያዩ ወረርሽኞችና ተላላፊ በሽታዎች መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

ገ) የወጣቶች ማዕከላት፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችና የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ጠ) የከተማ ነዋሪዎችን ልማታዊ ተሳትፎ ያሳድጋል፤ በተለይም የወጣቶችንና የሴቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ያጠናክራል፤ ያረጋግጣል እንዲሁም አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና አሳዳጊ የሌላቸው ህፃናት እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ጨ) የከተማውን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶች ዝግጅትና ትግበራውን ይከታተላል፤

ጸ) የከተማውን የትራንስፖርት አገልግሎት ያዘምናል፤ ለነዋሪዎች ተገቢውን አገልግሎት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

ጸ) በከተማው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ያረጋግጣል፤

ፀ) በአስተዳደር ወሰኑ ውስጥ የሚገኘውን የመሬት ይዞታን አያያዝ፣ አጠባበቅ

qoqqowu seerubanna stratejubba garinni massaganno;

ff) Woloota hasiissanno loossa loossanno.

3. Mootimmate loosaasine gashshooti seeri garinni loosaasine gashshitanno.
4. Konni quwira cinaancho quwa 2 woroonni tittirroonni assootenna owaantubba lifixa doogonni shiqishate ayee quchumi injiinoha ikke leelliro mootimmate, hallanya sekitere woy dancha fajjo uurinshubba ledo sheemaate e'anno; hattono dagate latishshi beeqqooshshi tantano kalaqanno.
5. Wodho agarsiissanno bissa tantana dandaanno. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.

FOOLIISHSHO SHOOLE

Quchummate Mootimmate Biilloonyi Bissa

13. Quchummate Mootimmate Biilloonyi Bissa

1. Rijiopolise, deerra mittunni kayse deerra sasu quchumma aante noo moottimmate biilloonyi bissa heedhannonsa:
   a) Quchumu amaale mini;
   b) Kantiiwu komite;
   c) Uurrrinshu yoote mine.
2. Deerra shoolunna deerra ontu quchummara aante noo bissa heedhannonsa:
   a) Quchumu ollii amaale mini
   b) Olluu gashshooti amaale mini
   c) Dagoomu yoo mini

አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓትን አግባብነት ያላቸው ሀገራዊና ክልላዊ ሕጎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ ይመራል፤

ፈ) ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. በመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ መሰረት ሰራተኞቹን ያስተዳድራል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራትና አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማቅረብ ማንኛውም ከተማ አመቺ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት፣ ከግሉ ሴክተር ወይም ከበጎ ፈቃደኛ ድርጅቶች ጋር ውል ይገባል፤ እንዲሁም የሕዝብ ልማት ተሳትፎ አደረጃጀቶችን ይፈጥራል፡፡
5. ደንብ አስከባሪ አካል ሊያደራጅ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

ምዕራፍ አራት

የከተሞች የመንግሥት የሥልጣን አካላት

13. በከተሞች የመንግሥት የሥልጣን አካላት

1. በሬጂዮ ፖሊስ፣ ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ ሶስት ከተሞች የሚከተሉት የመንግሥት ሥልጣን አካላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የከተማ ምክር ቤት፤
   ለ) የከንቲባ ኮሚቴ፤
   ሐ) መደበኛ ፍርድ ቤት፡፡
2. በፈርጅ አራትና ፈርጅ አምስት ከተሞች የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት፤

3. Konni quwi cinaanchu quwi 1 iima woroonnihu noo gedeenni heereenna lallawu quwa 41 garinni quchuma labbano hajubba gashshootu yoo mini hee'ransara dandaanno.

14. Quchumu Amaale Mine

1. Quchumu amaale mini doorshi gobbate doorshi seeri garinni gumulamanno.
2. Qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini mittu mittunku quchumi daga batinyenna doorshu mereershubba kaima assatenni quchumu amaale mini miilla batinye gumulanno.
3. Uminsa amaale mini noonsa quchumma giddo Sidaamu daga teessaano kiiro shiima ikkite leelturo qoqqowu mootimma amaalete mini Sidaamu daga teessaano wole daga ledo heewisiise quchumu amaale mini giddo 51% agarantannonsa gede assanno; tini woro olluu amaale minirano loosanno.
4. Uminsa amaale mini noonsa quchumu gashshooti giddo quchumu ledo danna xaaddanno baadiyyete olluubba quchumu amaale mini giddo 20% barcimi agaramannonsa.
5. Quchumu ledo danna xaaddanno baadiyyete woradda riqiwamaanonnino dooramaanote mereerinni olluu amaale mine riqiwantanno.
6. Quchumu amaale mini doorshira heewisamate shiqanno manchi gobboomu doorshu seeri safaraasine wonshannohanna qoqqowu loosu afoo dandaannoha ikka noosi.

ለ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፤

ሐ) ማኅበራዊ ፍርድ ቤት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች በአዋጁ አንቀጽ 41 መሠረት የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

14. ስለከተማ ምክር ቤት

1. የከተማ ምክር ቤት ምርጫ በብሔራዊ የምርጫ ሕግ መሠረት ይከናወናል፡፡
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የየከተማውን የሕዝብ ብዛትና የምርጫ ጣቢያዎችን መሠረት በማድረግ የከተማ ምክር ቤቱን አባላት ብዛት ይወስናል፡፡
3. የራሳቸዉ ምክር ቤት ባላቸዉ ከተሞች ውስጥ የሲዳማ ብሔር ነዋሪዎች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ ከተገኘ የክልሉ መንግሥት ምክር ቤት የሲዳማ ብሔር ነዋሪዎችን ብዛት ከሌላ ብሔረሰብ ብዛት ጋር በማነጻጸር ከከተማዉ ምክር ቤት መቀመጫ ውስጥ 51% እንዲጠበቅላቸው ያደርጋል፤ ይህ ድንጋጌ በቀበሌ ደረጃ ላለ ምክር ቤትም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤
4. የራሳቸው ምክር ቤት ባላቸው ከተሞች ከተማውን ለሚያዋስኑ የገጠር ቀበሌዎች በከተማው ምክር ቤት ውስጥ 20% መቀመጫ ይጠበቅላቸዋል፤
5. ከተማውን የሚያዋስኑ የገጠር አጎራባች ወረዳ ተወካዮችም ከተመራጮቹ መካከል በቀበሌ ምክር ቤት ይወከላሉ፡፡
6. ለከተማ ምክር ቤት ምርጫ ለመወዳደር የሚቀርብ ሰዉ የብሔራዊ የምርጫ ሕግ መስፈርቶችን የሚያሟላና የክልሉን የስራ

15. Quchumu Amaale Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha

1. Konni lallawi quwi 12 garinni quchumaho uynoonni billoonyinna loosu qeechi loosu aana hosanno gede assate biilloonyunna yawo hee'dhanosi.
2. Konni quwira cinaancho quwa 1 kullooniti xaphooma woro noo gedeenni hedheenna quchumu amaale minira konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi hee'rannosi:
   a) Bayriidi seerinni qoqqowu amaale minira uynoonni biilloonyi noo gedeenni hee'reenna Federaaletenna qoqqowoho fultino seerubbanni hanqafantinokki woy balaxxe fulitino seerubba jeefisate hasiissanno quchumma labbanno hajubba aana wodho woy biddissa fushshanno;
   b) Konni lallawnni bande uynoonni hajubba aana eo gamba assate hayyo gumulanno; gamba yaase buuxanno; hasiissanno taashsho assanno;
   c) Quchumu baatto seeru garinni galase buuxanno;
   d) Quchumu kantiiwa amaalete mini miillanni woy qeeltino poletiku paarte giddonni biiloonsanno;
   e) Kantiiwu shiqisheenna quchumu layinki kantiiwanna kantiiwu komite miilla biiloonsanno;
   f) Hasiishshansa amannoonnire uurrrinshu woy yannate geeshshi komite uurrrisanno; komittanniha loosu garano gumulanno;
   g) Konni lallawira uynoonni biilloonyi

ቋንቋ የሚችል መሆን አለበት፡፡

15. የከተማ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት ለከተማው የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ምክር ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) በሕገ-መንግሥቱ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራልና በክልል በወጡ ሕጎች ባልተሸፈኑ ወይም አስቀድሞ የወጡ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ከተማ ነክ ጉዳዮች ላይ ደንብ ወይም መመሪያ ያወጣል፤
   ለ) በዚህ አዋጅ ተለይተው በተሰጡ ጉዳዮች ላይ የገቢ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ይወስናል፤ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊ ማስተካከያ ያደርጋል፤
   ሐ) የከተማው መሬት በሕግ መሠረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፤
   መ) የከተማውን ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት ወይንም ከአሸናፊ የፖለቲካ ፓርቲ መካከል ይሾማል፤
   ሠ) በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ምክትል ከንቲባና የከንቲባ ኮሚቴ አባላት ይሾማል፣
   ረ) አስፈላጊነታቸው የታመነባቸውን ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤

garinni quchumu tantanonna gara kaajjishanno; kantiiwu shiqishanno hedo garinni loosu sooreeyye biiloonsa kaajjishanno;

h) Quchumu diru loosu mixonna baajete gumulanno, garunni loosu loosu aana hosaseno buuxanno;

i) Loosu massagaano keenantannota diru loosu jeefo bikkaanchonna timo wonsanno; Jeefishsha ha'rusanno; keenanno;

j) Gobbaaydi odiiterenni shallago qorqorsiisanno; odiitere shiqishshanno rippoorte kaiminni hasiissanno qaafo adhinanni gede assanno; Jeefishshano ha'runsanno.

k) Quchumu amaale mini miillara akatoommete wodho fushshanno; jeefisamaseno ha'runsanno; buuxanno;

l) Amaalete minira shiqqanno rippoorte aana hasaawe wonsanno;

m) Quchumaho qixxaabbino quchumu pilaane wonsanno; Jeefishshanoloosu ha'runsanno;

n) Kantiiwanna kantiiwu komite miilla hasiisiro xa'mote woshshanno.

16. Quchumu Amaale Mini Hundaanchimmanna Loosu Amanyoote

1. Quchumu amaale mini hundaanchimma doortinosi dagara ikkitanno.
2. Konni quwira cinaancho quwi 1 aana worroonnihu noo gedeenni hee'reenna polisubba; istrateejubbanna seerubbate

የኮሚቴዎችን የሥራ ሁኔታ ይወስናል፤

ሰ)በዚህ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የከተማውን አደረጃጀትና አወቃቀር ያጸድቃል፤ ከንቲባው በሚያቀርበው ሀሣብ መሠረት የሥራ ኃላፊዎችን ሹመት ያጸድቃል፤

ሸ) የከተማውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፤ በአግባቡ በሥራ መተርጎማቸውንም ያረጋግጣል፤

ቀ)ሥራ አመራሩ የሚመዘንበትን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም መለኪያና ግቦች ያጸድቃል፤ አፈፃፀምን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

በ)በውጭ ኦዲተር ሂሳቡን ያስመረምራል፤ ከኦዲተር በሚቀርበው ሪፖርት መነሻ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ተ) ለከተማው ምክር ቤት አባላት የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

ቸ) ለምክር ቤቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ ያፀድቃል፤

ኀ) ለከተማው የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖችን ያጸድቃል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ነ) ከንቲባውንና የከንቲባ ኮሚቴ አባላትን አስፈላጊ ሲሆን ለጥያቄ ይጠራል፡፡

16. የከተማ ምክር ቤት ተጠሪነትና የአሠራር ሥነ ሥርዓት

1. የከተማ ምክር ቤት ተጠሪነት ለመረጠው ሕዝብ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አንደተጠበቀ ሆኖ ፖሊሲዎችን፣

jeefishsha, eo gamba assanna woxu horoonsha lainohunni hundaanchimma doortinosi dagaranna qoqqowu mootimmara ikkitanno.

3. Amaalete miniti loosu yanna onte diro ikkite uurrinshunna wiinamu songo heedhannosi; Uurrinshu songo rijiopolisete quchumira shoolki shoolki aganira hadhanno; wole quchummara sasu sasu aganinni hadhanno.
4. Ayee amalete mini gambooshshira xaphooma miillanni lamunni sayikki anga aleenni ikkitannori leelturo songo wo'ma ikkitanno.
5. Ayee amaalete mini gambooshshira gumulo sa''a dandiitannohu gambooshshu aana leeltino miillanni bocu aleenni irkissurooti.

17. Quchumu Amaale Mini Billaalla

1. Quchumu daga hajote aana balaxxe amaalante gumultukkinni ayee quchumi amaale mini billaallara didandaanno.
2. Konni quwira cinaancho quwa 1 aana worroonnihu hee'rirono qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini teessaano daga horo gawajjannori woy bayriidi seeri amanyoote danote aana tugannoti jawa huno loosamase buuxiro quchumu amaale mine yannate geeshsha loosunni kie keeshshiishatenna hajo buuxate biilloonyi hee'rannosi. Kuni ikkanno woyte looso massagganno yannate geeshshi gashshooti somamanno.

ስትራቴጂዎችንና የሕጎችን አፈፃፀም፣ የገቢ አሰባሰብና የገንዘብ አጠቃቀምን በሚመለከት ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብና ለክልሉ መንግሥት ይሆናል።

3. የምክር ቤቱ የስራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤ ይኖረዋል፤ መደበኛ ጉባኤ በሬጂዮፖሊስ ከተሞች በየአራት ወሩ ይካሄዳል፤ በሌሎች ከተሞች በየሶስት ወሩ ይካሄዳል።
4. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ከጠቅላላ አባላቱ ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።
5. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ነው።

17. ስለ ከተማ ምክር ቤት መበተን

1. የከተማ ነዋሪ ሕዝብ አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ ሳይመክርበትና ሳይወስን የትኛውንም የከተማ ምክር ቤት መበተን አይቻልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የነዋሪውን ሕዝብ ጥቅም የሚነዳ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ከባድ ጥፋት መፈጸሙን ሲረዳ የከተማውን ምክር ቤት ለጊዜው ከሥራ አግዶ የማቆየትና ጉዳዩን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፤ ይህ በሚሆንበት አጋጣሚ ሥራውን የሚመራ ጊዜያዊ አስተዳደር ይሰይማል።

18. Yannate Geeshshi Quchumu Amaalaancho Amaale Mini Tantano

1. Ayee quchumino deerra sase sa”ano gede gumulliro dagate doorshini quchumu amaale mini uurra geeshsha qoqqowoho, woradaho, olluubate quchumunni doorantinori amaalete mini miilla hattono quchumuni uurritinorinna loosinsa akati quchumu loosi ledo lowontanni xaadisannonsa uurrinshubba loosu sooreeyyenna dagate tantano riqiwamaanonna egennantino mannooti miilla ikkitino yannate geshshi quchumu amaale mini massaganno gede assa dandiinanni. Tittirshu wodhotenni gumulamanno.
2. Haarote deerra sasu widira lophanno gede gumullooni quchumi yannate geeshshi kantiiwa quchumu yannate geeshshi amaale mininni biiloonsinanni.
3. Yannate geeshshi quchumu amaalaano amaale mini konni lallawi quwa 15 cinaancho quwa 2 (1-14) geeshsha xawinsoonni biilloonyinna loosu qeecha loosu aana hosiisate gobbaanni haaro seerubba fushsha, noo seerubba loosu aana hossannokki gede assa woy woyyeessa didandaanno.
4. Qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini deerra sasu quchumu gashshooti deerri widira sa’’anno gede gumulloonisi quchumi yannate geeshshi quchumu kantiibu komite heedhannosi.
5. Yannate geeshshi quchumu gashshooti kantiibi komite miilla moottimma kantiibu

18. ጊዜያዊ የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አወቃቀር

1. ማንኛውም ከተማ ወደ ፊርጅ ሶስት ደረጃ እንዲሸጋገር ሲወሰን በሕዝብ ምርጫ የከተማ ምክር ቤት እስኪቋቋም ድረስ የክልል፣ ለወረዳ፣ ለቀበሌ ከከተማው ከተመረጡት የምክር ቤት አባላት እንዲሁም በከተማው የተቋቋሙና የሥራ ባህርያቸው ከከተሞች ሥራ ጋር የበለጠ የሚያገናኛቸው ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እና የሕዝብ አደረጃጀቶች ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦች አባል የሆኑበት ጊዜያዊ የከተማ ምክር ቤት እንዲመራ ሊደረግ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. አዲስ ወደ ፊርጅ ሶስት ደረጃ እንዲያድግ የተወሰነለት ከተማ ጊዜያዊ ከንቲባ በከተማው ጊዜያዊ ምክር ቤት ይሾማል፡፡
3. ጊዜያዊ የከተማ አማካሪ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 (1-14) የተደነገገውን ሥልጣንና ተግባር ከመተግበር በስተቀር አዲስ ሕጎችን ማውጣት፣ ነባር ሕጎችን መሻር ወይም ማሻሻል አይችልም፡፡
4. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወደ ፊርጅ ሶስት የከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲሸጋገር የተወሰነለት ከተማ ጊዜያዊ የከተማ ከንቲባ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡
5. ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር ከንቲባ ኮሚቴ አባላት ሹመት በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ጊዜያዊ ምክር ቤት ይጸድቃል፡፡
6. በከተማው የተቋቋሙና የሥራ ባህርያቸው ከከተሞች ሥራ ጋር የበለጠ የሚያገናኛቸው ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች የከተማ ከንቲባ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

shiqisheenna quchumu yannate geeshshi amaale mini wonsanno.

6. Quchumaho uurritinorinna loosu akatinsa quchumu loosi ledo roore xaadisannonsa uurrinshubba loosu sooreeyye quchumu kantiibi komite miilla ikitanno; Tittirshu wodhotenni gumulamanno.
7. Yannate geeshshi kantiibu komite biilloonyinna loosu qeechi konni lallawi quwa 21 cinaancho quwa 4 kiiro (2) kayse (9) geeshsha xawinsoonniha ikkanno.
8. Yannate geeshshi kantiibu biilloonyinna loosu qeecha lainohunni konni lallawi quwa 21 cinaancho quwa 1 kiiro (2) kayse kiiro (13) geeshsha hattono konni lallawi quwa 12 cinaancho quwa 2/1/nna (3) kayse /31/ geeshshanna cinaancho quwa 3,4, nna 5 aana leellanno looso loosanno.
9. Konni lallawira kantiiwu komiteranna kantiiwaho xawinsoonni hundaanchimma hasiisanno garinni yannate geeshshi kantiiwi komiteranna yannate geeshshi kanitiiwira loosu aana hossannota ikkitanno.
10. Yannate geeshshi amaalaancho amaale mini songaafich, layinki songaaficho somama; hundaanchimma, biiloonyinna loosu qeechi konni lallawi quwi 19 xawinsoonni garinni ikkanno.

19. Quchumu Amaale Mini Songaafichanna Layinki Songaaficha Somama, Biilloonyenna Loosu Qeecha

1. Amaalete mini songaafichinna layinki songaafichi qeeltino poletiku paarte miillanni

7. የጊዜያዊ ከንቲባ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 4 ከቁጥር (2) እስከ ቁጥር (9) የተመለከተው ይሆናል፡፡

8. የጊዜያዊ ከንቲባ ሥልጣንና ተግባር በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ(2) እስከ (13) እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 (1)፣ ከ(3) እስከ (31) እና ንኡስ አንቀጽ 3፣ 4 እና 5 የተመለከቱትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. በዚህ አዋጅ ለከንቲባ ኮሚቴ እና ለከንቲባ የተደነገገው ተጠሪነት እንደአግባብነቱ ለጊዜያዊ ከንቲባ ኮሚቴ እና ለጊዜያዊ ከንቲባው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10. የጊዜያዊ አማካሪ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ አሰያየም፣ ተጠሪነት ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው አግባብ ይሆናል፡፡

19. የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ አሰያየም፣ ስልጣንና ተግባር

1. **የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ከአሸናፊ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጥ ሆኖ ተጠሪነቱም ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡**
2. **የምክር ቤቱ አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡**
3. **የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-**
   - **ሀ) የምክር ቤቱን የመወያያ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤ ስብሰባዎችን ይመራል፤**
   - **ለ) ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ በቋሚና**

amaalete mini miilla mereerinni doorranniha ikke hundaanchimmano amaalete minira ikkitanno.

2. Amaalete mini songaafichinna layinki songaafichi loosu yanna amaalete mini loosu yanna ikkitanno.
3. Amaalete mini songaafichira aane noo biilloonyenna loosu qeechi hee'rannosi:
   a) Amaalete mini hasawu ajenda qixxeessanno; songo massaganno;
   b) Amaalete mini hasiishshu garinni uurrinshunna yannate geeshshi komite tantanantanno hayyo kalaqanno; mixi'ranno; loosu aana hosase ha'runsanno;
   c) Uurrinshunna yannate geeshshi komitenni shiqqanno rippoorte keene gumulote hedo amaalete minira shiqishanno; gumulsiisanno;
   d) Miillate aana adhinannita disipiliinete qaafo jeefisiisanno;.
   e) Amaalete mini miillata dhuka bowirsate loosi mixo qixxeessanno; hajo la'annonsa jeefisiisaano ledo qinaawe jeefisiisanno;.
   f) Amaalete mini gumulo yannatenni hajo la'annonsa loosu bissara iillitanno gede assanno; loosu aana hosansa ha'runsanno;
   g) Sayikki bisi ledo assinanni xaadira amaalete mine riqiwanno;
   h) Amaalete mininni uynanni woloota loossa loosanno.
4. Amaalete mini layinki songaafichi biilloonyenna loosu qeecha፡

በጊዜያዊ ኮሚቴ የሚደራጅበትን ስልት ይነድፋል፤ ያቅዳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሐ) በቋሚና በጊዜያዊ ኮሚቴ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ያስወስናል፤

መ) በአባላት ላይ የሚወሰደውን የዲሲፕሊን እርምጃዎች ያስፈጽማል፤

ሠ) የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፤

ረ) የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በወቅቱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲተላለፉ ያደርጋል፤ ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፤

ሰ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፤

ሸ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

4. የከተማው ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት፡-
   ሀ) ዋና አፈ ጉባኤ በሌለበት ተክቶት ይሰራል፤
   ለ) በዋናው አፈ ጉባኤ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

20. የከንቲባ አሰያየም፣ ተጠሪነትና የሥራ ዘመን

1. አሰያየም
   ሀ) ከንቲባው ከምክር ቤቱ አባላት ወይንም ከአባላት ውጭ በአሸናፊ የፖለቲካ

a) Qaru songaafichi nookkiwa riqiwe loosanno;

b) Qaru songaafichinni bande uynannisi woloota loossa loosanno.

20. **Kantiiwu Somama; Hundaanchimmanna Loosu Yanna**

1. Somama

